# “የነፃነት ማጎሪያዎች” በኤርትራ

**ዘሪሁን በየነ 12-26-14**

ይህን ፅሑፍ ሳዘጋጅ አንድ በአንድ ወቅት ያነበብት አፈ-ታሪክ ትውስ አለኝ። አፈ-ታሪኩ ላዘጋጀው ካሰብኩት ፅሑፍ ጋር መሳ ለመሳ የሚሄድ በመሆኑ የጥንቅሬ መግቢያ ላደርገው ወደድኩ። ነገሩ እንዲህ ነበር።…

…ወቅቱ ከመጀመሪያው የዓለም ጦርነት በፊት ነው፡፡ ታዲያ በዚያን ጊዜ ይኖሩ የነበሩ አንድ ንጉሥ ነበሩ፡፡ በእኚህ ንጉሥ ዙሪያ የሚነገሩ በርካታ አፈ-ታሪኮች አሉ። ከአፈ ታሪኮቹ ውስጥ አንዱ የንጉሡ የጭካኔ ተግባር ነው፡፡ ንጉሱ የሀገሩን ህዝብ እየዞሩ በነፍስ ወከፍ ግብር ያስገብሩት ነበር አሉ፡፡ በመሐሉ ግን ግብር አንገብርም የሚሉ ሰዎች እየተበረከቱ መምጣታቸውን ምስለኔዎቻቸው ሹክ ይሏቸዋል።

ሁኔታው ለምን እንደተፈፀመ ከመመርመር ይልቅ በቁጣ የጦፉት ንጉሱ የጭካኔ ውሣኔ ያስተላልፋሉ፡፡ በመሆኑም ግብር አንከፍልም ያሉ የዚያች ሀገር ዜጎች ሳር ቤት ውስጥ ገብተው እንዲቃጠሉ ያዛሉ፡፡ ለዚህ ተግባር የሚውሉም በርካታ የማጎሪያ እስር ቤቶች እንዲዘጋጁም አስደረጉ፡፡ አጋፊሪዎቻቸውም በአንድ ሳር ቤት ውስጥ ስልሳ ሰዎችን እያስገቡ እንዲያቃጥሉ ቀጭን ትእዛዝ ያስተላልፋሉ፡፡

ትዕዛዙም መተግበር ጀመረ፡፡ አንድ ቀን ግን እንደ አጋጣሚ ሆኖ በዕለቱ ከሚቃጠሉት ስልሳ ሰዎች ውስጥ አምሳ ዘጠኝ ብቻ ይገኛሉ፡፡ እናም ንጉሡ ትዕዛዛቸው ተፈጻሚ መሆኑን ለመመልከት ሲዘዋወሩ ጠባቂው “ጌታዬ የዛሬዎቹ አምሳ ዘጠኝ ብቻ ናቸው፣ ምን እናድርጋቸው?” ሲል ይጠይቃል፡፡ ንጉሡም ዙሪያ ገባውን ገልመጥ፣ ገልመጥ አደረጉና “ታዲያ አንተ ምን ትሰራለህ?” ብለው ጠባቂውን ስልሳኛ በማድረግ ሳር ቤት ውስጥ ገፍትረው ካስገቡት በኋላ አቃጠሉት ይባላል፡፡…

እርግጥ ይህን እጅግ ጥንታዊ አፈ-ታሪክ የነገሬ ራስ ያደረኩት ዝም ብዬ አይደለም-ሰሞኑን ኤርትራ ውስጥ እየተፈፀመ ያለው ዘግናኝ ግፍ በገሃድ ይፋ መሆኑን ተከትዬ እንጂ። ያኔ ዘመኑ ሩቅ፣ ጊዜውም የሰው ልጅ አስተሳሰብ ያልሰለጠነበት ነበር፡፡ በዚያን ጊዜ ነገሩ ሁሉ "ንጉሥ አይከሰስ፣ ሰማይ አይታረስ" ነውና የንጉሡ ተግባር ዘግናኝ የጭካኔ ድርጊት ቢሆንም፣ ትዕዛዙ ተፈፃሚ መሆን እንዳለበት ግን ይታመናል፡፡ በአንጻሩ፣ ዛሬ ዓለም በዘመነበት፣ ችግሮች ሰላማዊና ዴሞክራሲያዊ በሆነ በሰለጠነ የጠረጴዛ ዙሪያ መንገድ በሚፈቱበት እንዲሁም እስር ቤቶችና ግድያዎች እንደመፍትሔ በማይታዩባት ዓለማችን፣ በሀገረ ኤርትራ በሻዕቢያ አማካኝነት እየተፈፀመ ያለው የግፍ፣ የሠቆቃና የግድያ ተግባር ግን ከአደኛው የዓለም ጦርነት በፊት የነበሩትን የንጉሡን አፈ-ታሪክ የሚያስታውሰን ነው የሆነው፡፡ እናም ድርጊቱ ሰላም ወዳድ ኃይሎችን እያነጋገረ ነው፡፡

ሻዕቢያ ኢትዮጵያን በዕብሪት መውረሩ ትክክል ያለመሆኑን፣ በሀገሪቱ ውስጥ ሰብዓዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶች እንዲከበሩ እንዲሁም የአምባገነኑ ኢሳያስ አፈወርቂ አገዛዝ እንዲያበቃ ሲወተውቱ የነበሩ የሀገሪቱ የቀድሞ ከፍተኛ ባለሥልጣናት፣ ጋዜጠኞችና ዜጎች፣ የአቶ ኢሳያስ መንግሥት በተለያዩ የሀገሪቱ ከባቢዎች በፈጠራቸው "ጓንታናሙ ቤይ" ማጎሪያዎች ውስጥ እየማቀቁ መሆኑን ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች የዓይን አማኞችን በመጥቀስ እየገለፁ ነው፡፡

እርግጥ በዓለማችን የህዝቦችን ጥያቄ አንግበው፣ "ዱር ቤቴ" ብለው፣ ለዓመታት ተዋድቀውና ኋላም በድል ተመልሰው ህዝቦቻቸውን በተፈለገው የለውጥ ጎዳና ላይ ለማራመድ የቻሉ ቁራጥ ህዝባዊ ታጋዮች እንዳሉ ሁሉ፣ የዓመታት የህዝቦችን የነፃነት ተጋድሎ ትርጉም በማሳጣት በህዝባቸው ላይ ዳግም የጭቆና እና የግፍ ቀንበርን የጫኑ ዓላማ ቢሶችም ታይተዋል፡፡

ኤርትራ ውስጥ አምባገነኑን የደርግ ስርዓት በአምሳያ የተካው የአቶ ኢሳያስ የግፍ አገዛዝም፣ ከእነዚህ ዓላማ ቢሶች ውስጥ በግንባር ቀደምትነት የሚጠቀስ ኃይል ነው፡፡ ሻዕቢያ ከ1993 ዓ.ም ጀምሮ ለአስራ ሁለት ዓመታት ያለምንም ጥያቄና ፍርድ ኮንቴይነር ውስጥ አጉሮ ያሰቃያቸው የነበሩት 35 ከፍተኛ የሀገሪቱ የቀድሞ

ባለሥልጣናት እና ጋዜጠኞች የአቶ ኢሳያስ አስተዳደር ዓላማ ቢስ መሆኑን የሚያረጋግጡ ናቸው፡፡

የነፃነት ታጋዩ አቶ ኢሳያስ ዓላማቸውን ስተው "ታግዬለታለሁ" የሚሉት የገዛ ህዝባቸውን በግፍ ቋያ እሳት እየለበለቡት መሆኑ አንሷቸው አጠገባቸው የነበሩትን ባለስልጣኖቻቸውን፣ ሰው ቀርቶ እንሰሳ በማይታሰርባቸው እስር ቤቶች ውስጥ አጉረው ማሰቃየታቸው ሰውዬው "ነፃ አውጪ" ማይሆኑ ፀረ-ነፃነት መሆናቸውን በገሃድ እያስመሰከሩ ነው፡፡ "አብዮት ልጆቿን ትበላለች" ይል ነበር- ያኔ ድሮ ሰው በላው የደርግ ስርዓት መሪ- አጠገቡ ያሉትን የስልጣን ተቀናቃኞቹን ለመፍጀት ሲፈልግ፡፡ አቶ ኢሳያስም አጠገባቸው የነበሩ ፍትሕና ርትዕ ፈላጊዎችን በማሰር፣ በመደብደብ፣ ህክምና ባለመስጠት እንዲሁም በረሃብ እንዲሞቱ በማድረግ በእስር ቤቶቻቸው በጉያቸው አቅፈዋቸው የነበሩትን "ልጆቻቸውን" ሲበሉ የከረሙት፡፡

ሻዕቢያ ይህንን ግፍ የሚፈጽምበት ዋነኛ ማጐሪያዎቹን "ኢራኢሮ"፣ "ቤት መሓጐስ" እና "እምባትካላ" እያለ ይጠራቸዋል፡፡ ልብ በሉ! እንግዲህ እነዚህ ቦታዎች እጅግ ከፍተኛ ሙቀት ያለባቸው፣ ከፍተኛ ቁጥር ያላቸው ሰዎች በትንንሽ ኮንቴይነሮች ውስጥ የሚታጨቁባቸው እንዲሁም የሰው ልጅ ራሱን እስኪጠላ ድረስ በድብደባ የሚሰቃይባቸው የሻዕቢያ "ጓንታናሙ ቤይ"ዎች መሆናቸው ነው፡፡

ስለ "ጓንታናሞ ቤይ" ሳነሳ አንድ ሀገርኛ ዜይቤያዊ አባባልን አስታወስን፡፡ ይኸውም "በራስህ ዓይን ውስጥ ያለውን ትልቅ ግንድ ሳታይ፣ በሰው ዓይን ውስጥ ያለውን ጉድፍ ለማውጣት አትሞክር" የሚል ነው፡፡ ሻዕቢያ "አሜሪካ አሸባሪዎችን ታሰቃያለች" በሚል "ጓንታናሙ ቤይ ውስጥ እንዲህ ተደረገ፣ እንዲህ ሆነ፣ እገሌ ተደበደበ… ወዘተ" እያለ ተመልካች እስኪሰለቸው ድረስ የሀሰት ፕሮፖጋንዳ በሚያሰራጭበት ቴሌቪዥኑ በየዕለቱ ይለፍፋል፡፡ በአንድ ወገን፣ ለህዝቡ መረጃ የሚሰጥ እየመሰለ ይህን የ"ጓንታናሙ ቤይ"ን ዘግናኝ ድርጊት እንደ "ውዳሴ ማርያም" እየደጋገመ ሲያቀርብ፣ በሌላ በኩል ደግሞ የራሱን "ጓንታናሙ ቤይ" ፈጥሮ ህዝቡን ያሰቃያል፡፡

የሻዕቢያውና የአሜሪካው “ጓንታናሙ ቤይ”ዎች ልዩነት አላቸው፡፡ እርግጥ አሜሪካ በኩባ ግዛት ከባቢ በሚገኘው በ“ጓንታናሙ ቤይ” ደሴት ውስጥ ታሰቃያቸዋለች እየተባለ የሚነገረው ከመስከረም አንድ ጥቃት ጋር በተያያዘ የሚጠረጠሩ አሸባሪዎችንና ከአልቃይዳ ጋር ግንኙነት ያላቸውን ጽንፈኞችን ነው፡፡ ሻዕቢያ ግን መንበረ ስልጣኑን ለማደላደል ሲል “ቆሜለታለሁ” የሚለውን የገዛ ህዝቡን ነው እስር ቤት ውስጥ እያሰቃየ በረሃብና በህክምና እጦት እንዲሞቱ የሚያደርገው፡፡

በመሆኑም ሻዕቢያ ዓይኑ ስር ያለውን እንደ ግንድ የገዘፈ “ጓንታናሙ ቤዩን” ሳያይ፡ በሌላው ላይ ጣቱን መቀሰሩ ያው የተለመደ የማደናገሪያ ዘዴው መሆኑ ከማንም የተሰወረ ጉዳይ አይደለም፡፡ እርግጥ ተመልካቹን ያታከተው የሻዕቢያው የውሸት ዘገባ ፈብራኪ ቴሌቪዥን የ“ጓንታሙ ቤይ” ፕሮግራም ግቡ ሁለት ነው፡፡ አንደኛው “እንኳንስ እኛ ቀርቶ ዴሞክራሲያዊና ሰብአዊ መብቶችን አክብሬአለሁ የምትለው አሜሪካም ታሰቃያለች” የሚል እንደምታ ያለው ሲሆን፣ ሁለተኛው ደግሞ ህዝቡ በሻዕቢያ ላይ የሸፈቱ የቀድሞ ባለሥልጣናትንና ዜጎችን መስመር እንዳይከተል በማስፈራራት የግፍ አገዛዙን አጠናክሮ ለመቀጠል የታለመ ነው፡፡

ይሁንና የሻዕቢያን የግፍ ተግባር በቅርበት ሲከታተሉት የነበሩት የኤርትራ ህዝቦች ዲሞክራሲያዊ ፖርቲ ሊቀመንበር አቶ ወልደየሱስ አማረ ሰሞኑን ለተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ዋና ፀሐፊ ለሚስተር ባን-ኪሙን የተማፅኖ ደብዳቤ ጽፈዋል፡፡

በደብዳቤያቸውም፣ በሀገረ ኤርትራ በእስር ላይ የሚገኙ የቀድሞ ባለሥልጣናት መሞታቸውን፣ ግድያና ግፍ እንዲሁም መከራ እየተባባሰ መምጣቱን በመግለጽ የመንግሥታቱ ድርጅትና የሚመለከታቸው ወገኖች ሁኔታውን እንዲያጣሩ ጠይቀዋል፡፡ በዚያች ሀገር የሚገኙ የማጐሪያ እስር ቤቶች በገለልተኛ ወገኖች እንዲጐበኙ፣ የፖለቲካ እስረኞች ለፍርድ እንዲቀርቡ፣ ከተቻለም እንዲፈቱ በአጽንኦት ይጠይቃሉ- አቶ ወልደየሱስ፡፡

አዎ! የሻዕቢያ “ጓንታናሙ ቤይ”ዎች ከ30 ሺህ የማያንሱ የፖለቲካ እስረኞች የታጐሩባቸው ድብቅ የምድር ቤት እስር ቤቶች ናቸው፡፡ እስር ቤቶቹ ውስጥ ምን እየተፈፀመ መሆኑን ከጥቂት የፀጥታ ሰራተኞች በስተቀር ማንም የሚያውቅ የለም፡፡

በረሃብ፣ በድብደባና በህክምና እጦት ምክንያት ሰዎች ሲሞቱም አስከሬናቸው የት እንደሚወሰድ ማንም አያውቅም፡፡ ከደርግ አምባገነንነት ወደ ሻዕቢያ አምባገነንነት የተሸጋገረው የዚያች አዲስና ወጣት ሀገር ህዝብ፣ ትምህርት ቤት የሚገነባለት ልማታዊ መንግሥት በማጣቱ፣ እነሆ በየጥሻውና በየበረሃው በተዘጋጁ እስር ቤቶች ውስጥ መታጐር ሆኗል-ዕጣ ፈንታው፡፡

የኢትዮ-ኤርትራ ጦርነት  በኢትዮጵያ ድል አድራጊነት መደምደሙን ተከትሎ በተነሳው የጦርነቱን ፍትሐዊነትና የፕሬዚዳንቱን አምባገነናዊ አገዛዝ የማብቃት ጥያቄ ሳቢያ፤ በኢሳያስ አፈወርቂ ትዕዛዝ ወደ ሻዕቢያ "ጓንታናሙ ቤይ" ዘብጥያ እንዲወርዱ ከተደረጉት 35 የቀድሞ ከፍተኛ ባለሥልጣናት ውስጥ 15ቱ በህክምና እጦት ፣ በረሃብና በድብደባ ስቃይ እንዲሁም በከባቢው ባለው ከፍተኛ ሙቀት ህይወታቸው አልፏል፡፡

"ኢራኢሮ" ይባላል- ዋነኛው የሻዕቢያ ጉረኖ፡፡ ይህ እስር ቤት ከአስመራ ከተማ በስተሰሜን በቀይ ባህር ከባቢ የሚገኝ ከፈተኛ ሙቀት ያለበት ቦታ ነው፡፡ በዚህ እስር ቤት ውስጥ ከሚሞቱት እስረኞች በተጨማሪ፣ ከሚደርስባቸው ስቃይ ለመገላገል ራሳቸውን የሚያጠፉ ኤርትራውያን ቁጥርም ከፍተኛ ነው፡፡

በዚህ የሻዕቢያ  "ጓንታናሙ ቤይ" ውስጥ ህይወታቸው ካለፉት ሰዎች መካከል የቀድሞው የሀገሪቱ ምክትል ፕሬዚዳንት አቶ መሀመድ ሸሪፎ እንዲሁም ጄኔራል ዕቁባይ አብርሃ እና አምስት ጋዜጠኞች ይገኙበታል፡፡ እነዚህ የያኔዎቹ የኢሳያስ አፈወርቂ "የቀኝ እጆች"  ሆነ ተብሎ ህክምና እንዳያገኙና በቀን አንዴ ዳቦ በውሃ እንዲመገቡ በመደረጋቸው እንዲሁም ከባድ ድብደባ ስለደረሰባቸው በሻዕያ ስውር የበቀል ሰይፍ ህይወታቸውን እንዲያጡ ተደርጓል፡፡ "አብዮት ልጆቿን ትበላለች" ይሏል የደርጉ አምሳያ ሻዕቢያ እንዲህም አይደል?

ከህዝቡ ጫንቃ ላይ አልወርድም ያሉትና በአንድ ወቅት ለጋዜጠኞች "ከእኔ በኋላ ኤርትራን ማን እንደሚመራት እንኳንስ እኔ እግዚአብሔርም አያውቅም" በማለት ሳያስቡት ማንነታቸውን ገሃድ ያወጡት አቶ ኢሳያስ፣ ምክትላቸው የነበሩትን አቶ መሀመድ ሸሪፎን እስር ቤት ውስጥ አሰቃይተው መግደላቸው የመጽሐፍ ቅዱሱን የማቱሳላን እድሜ ተውሰው ኤርትራን ለዘመናት ለመግዛት ያስቡ አስመስሏቸዋል፡፡

ይሁንና እንኳንስ እንደርሳቸው አይነት ከበረሃ ጀምሮ በተጠናወታቸው ፀረ-ዴሞክራሲያዊ አስተሳሰብ ለህዝባቸው ሳይሆን ለራሳቸው አስተሳሰብ የበላይነት ሲሉ የገዛ ጓደኞቻቸውን በረሃብና በድብደባ የሚገድሉ አምባገነን መሪ ቀርቶ፣ ቻይናን ከጨቋኙ ዘውዳዊ አገዛዝ አላቀው የሰፊውን አርሶ አደር ጥያቄ በመምራት ወደ ዛሬው የእድገት እንድትመራ ያደረጓት ማኦ ሴቱንግ እንኳን የህዝባቸው ባለውለታ ሆነው ሳለ ስልጣናቸውን በፈቃዳቸው ለተተኪዎቻቸው አስረክበው አልፈዋል፡፡ ዳሩ ግን አምባገነኖች ከዚህ ውጭ ሊያስቡ አይችሉም፡፡

ለዚህም ነው አቶ ኢሳያስ ለወንበራቸው ሲሉ ህዝባቸውን በየማጐሪያው አፍነው በማሰቃየት ለህልፈተ -ህይወት የሚዳርጉት፡፡ ለነገሩ ኢሳያስ አፈወርቂ ሰዎችን በማጐሪያ ውስጥ አፍኖ የመግደል ዘዴን የጀርመን ፋሽታዊ ገዥ ከነበረው ከመንፈስ አባታቸው ከአዶልፍ ሂትለር ሳይማሩት የቀሩ አይመስለኝም፡፡

ያም ሆነ ይህ “ማን ይናገር የነበረ...” እንዲሉ ነውና ብሂሉ፣ በአንድ ወቅት ከኤርትራ ወደ ኢትዮጵያ አምልጠው የመጡት የ35 ዓመቱ ጐልማሳ አቶ ኢዮብ ባህታ ስለ ሻዕቢያ “ጓንታናሙ ቤይ” ይናገራሉ፡፡ እኚህ ግለሰብ “ኢራኢሮ” እና “እምባትካላ” የሚባሉ የአቶ ኢሳያስ ማጐሪያዎችን ሲጠብቁ የነበሩ ናቸው፡፡

መቼም ትረፊ ያላት ነፍስ ናትና በመግቢያችን ላይ እንደጠቀስናቸው ንጉሥ እስር ቤት ጠባቂ በሻዕቢያ የበቀል ሰይፍ አልተቀሉም፡፡... እናም ማጐሪያዎቹን እንዲህ ይገልጿቸዋል፡፡ አቶ ኢዮብ እንደሚናገሩት፣ ቀደም ሲል ከጠቀስናቸውና በ“ኢራኢሮ” እስር ቤት ከታሰሩት 35 የቀድሞ የሀገሪቱ ከፍተኛ ባለስልጣናት ውስጥ 15ቱ ሞተው 20 ብቻ ቀርተዋል፡፡ ከ20ዎቹ ውስጥም ዘጠኙ በደረሰባቸው እጅግ አሰቃቂ ድብደባ ምክንያት አካላቸው ጐድሏል፣ ለአእምሮ መታወክና ለሌሎች በሽታዎችም ተጋልጠዋል፡፡

በኢትዮ-ኤርትራ ጦርነት ወቅት እ.ኤ.አ በ2000 ኤርትራ በመወከል ከኢትዮጵያ ልዑክ ጋር አልጀርስ ላይ የተፈራረሙት የቀድሞው የሀገሪቱ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር አቶ ኃይለ ወልደተንሳይ በደረሰባቸው ዘግናኝ ድብደባ ምክንያት ሁለቱም አይናቸው

ጠፍቷል፡፡ሌሎች እስረኞችም 24 ሰዓት እጅና እግራቸው በካቴና ተጠፍሮ ዕለተ-ሞታቸውን እየተጠባበቁ መሆናቸውን የዓይን እማኙ ያስረዳሉ፡፡

እርግጥ ሻዕቢያ የግፍ፣ የሰቆቃና የግድያ ተግባር በዜጐቹም ይሁን ጉዳዩን በሚያውቁ ወገኖች ተዘርዝሮ የሚያልቅ አይደለም፡፡ ህዝቡን የሚያሰቃይባቸው "ጓንታናሙ ቤይ ዎች"ን ለአብነት ያህል አነሳን እንጂ፣ የአቶ ኢሳያስን አምባገነናዊ አስተዳደር የሠቆቃ አሰራሮች በዚህ አጭር ጽሁፍ ለመቋጨት የሚሞከር አይደለም። ይልቁንም ሰውዬው በገዛ ህዝባቸው ላይ የሚፈጽሙትን ፀረ-ሰላም፣ ፀረ-ልማትና ፀረ-ዴሞክራሲ ተግባር ለመዘርዘር በርካታ ድርሳኖች ሳያስፈልጉ አይቀርም፡፡ እስቲ ጥቂቶቹን እንይ።...

..."የ29 ዓመቱ ዮሐንስ እምባዬ ሙሉ ፈገግታ አይታይበትም፤ በስሱ ብቻ ነው ፈገግ የሚለው። የታመቀ ድምጹ ውስጣዊ ብሶቱን ከመግለጽም በላይ፣ ስሜት አልባ ቡናማ መሳይ ዓይኖቹም የውስጡን የተጻፈነ የሰቆቃ ረመጥ ያሳብቃሉ፡፡

ኡጋንዳ ውስጥ በጥገኝነት የሚኖረው ይህ ወጣት፣ ለስድስት ወራት ያህል የታሰረበትን እስር ቤት ሽንት ቤቱን በምድር ውስጥ ለውስጥ ቆፍሮ ከኤርትራ አሰቃቂ እስር ቤቶች ያመለጠ ነው፡፡ 30 የሚሆኑ የሀገሪቱ ጋዜጠኞች በህገ-ወጥ መንገድ የሻዕቢያ ማጎሪያዎች ውስጥ እየተሰቃዩ መሆናቸውን ሲናገር ፊቱ ላይ የሚያጠላው የሀዘን ድባብ ልብን ይሰብራል፡፡"...

...ኤርትራ ውስጥ "ሓዳስ ኤርትራ" እየተባለ ለሚጠራው ጋዜጣ ይሰራ የነበረው ዮሐንስ ከአሥመራ 10 ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ የሚገኘው "ዓዲ ነፋሲት" እሥር ቤት ውስጥ ለስድስት ወራት ከታሰረ በኋላ፤ የእሥር ቤቱን ሽንት ቤት ያለመታከት ለስድስት ወራት ያህል ከምድር በታች ውስጥ ለውስጥ በመቆፈር ማምለጡን በከፍተኛ ሀዘን ተውጦ ይናገራል፡፡ በዚያ እሥር ቤት ውስጥ ይሰራበት የነበረው ጋዜጣ ዋና አዘጋጅ አቶ ሰዒድ አብዱልቃድር በድብደባ ስቃይ ብዛት መሞታቸውን ሲናገርም ፊቱን ቅጭም አድርጎ ነው። ይህ ዘገባ የዚህ ጽሑፍ አቅራቢ አይደለም - ጋዜጠኛ ዮሐንስ እምባዬ በአንድ ወቅት ለተለያዩ የመገናኛ ብዙሃን የሰጠው ቃለ -ምልልስ እንጂ፡፡ መገናኛ ብዙሃኑ የጋዜጠኛውን ከእሥር ቤት የማምለጥ ሁኔታን "ፕሪዝን

ብሬክ” እያሉ ቢገልጹትም፣ ጋዜጠኛው ግን የአቶ ኢሳያስ መንግስትን እስር ቤቶች በምሬትና በጸጸት ነው የሚያስታውሳቸው፡፡

ሉዓላዊ ነጻነት የከፈሉት መስዋዕትነት ሀገሪቱን የዛሬ 21 ዓመት ገደማ “ነጻ” ቢያወጣትም፣ መስዋዕትነቱ የነጻነት ትግሉ ለወለደው አንድ አምባገን ቡድንና መሪ አሳልፎ ከመስጠት ሌላ ያስገኘላቸው አንዳችም ውጤት የለም፡፡ ኤርትራውያን “ከነጻነት” በኋላ ለሀገራቸው “ይሆናል” ብለው አስበውትና ተመኝተውት የነበረው “ነፃነት” ዛሬ እንደ ጉም በኖ ጠፍቷል፡፡

ሻዕቢያ በትጥቅ ትግል ወቅት የነበረው ተደማጭነት ዘለዓላማዊ መስሎትና የልብ ልብ ተሰምቶት፣ እነሆ “ታገልኩለት፣ አታገልኩት፣ ነጻነት ሰጠሁት” የሚለውን ህዝብ “ነጻነት” አግቶ ይገኛል፡፡ ይሁንና ኤርትራውያን ይህን የተነጠቁትን ነጻነት ለማስመለስ እየተሯሯጡ ነው፡፡ ከዚህ አንጻር ነፍጥ አንግበው “ዱር ቤቴ” ያሉትን የቀይ ባህር አፋሮችንና ኩናማዎችን መጥቀስ ይቻላል፡፡

ሠላማዊው ህዝብ ደግሞ የጎረቤት ሀገሮችን ድንበር እያቋረጠ ከሻዕቢያ እሥር ቤቶች መንጋጋ ለማምለጥ ጥረት ያደርጋል፡፡ በለስ የቀናቸው ወደ ጎረቤት ሀገሮች ሲዘልቁ፣ ያልተሳካላቸው ደግሞ የሻዕቢያ የጥይት አረር ሰለባ ይሆናሉ፡፡ “ሱዳን ትሪቡን” የተሰኘው ዕለታዊ የሱዳን ጋዜጣ በአንድ ወቅት እንደዘገበው ፣ ከኤርትራ ጋር አዋሳኝ በሆኑ የሀገራችን ካምፖች ውስጥ እስካሁን ድረስ በርካታ ኤርትራውያን ስደተኞች ይገኛሉ፡፡

ከእነዚህ ውስጥ የኤርትራ መከላከያ ሠራዊት አባላትና አብዛኛዎቹም ወጣቶች መሆናቸውን ዘገባው ያመለክታል፡፡ የአቶ ኢሳያስን የግፍ አገዛዝ፣ እስርና እንግልት በመፍራትም በየወሩ በአማካይ 1 ሺህ 800 ኤርትራውያን የኢትዮጵያን ድንበር እያቋረጡ እንደሚገቡም እንዲሁ አትቷል፡፡

የአስመራውን ፈላጭ ቆራጭ አስተዳደር አገዛዝን በቅርበት የሚያውቁት ምንጮች እንደሚናገሩት፣ በሻዕቢያ ላይ የሰላ ሂስ የሚሰነዝሩ ዜጎች፣ የሃይማኖት አባቶችና በተቃዋ ሚነት የተሰለፉ ኤርትራውያን ቁጥራቸው ከጊዜ ወደ ጊዜ እያሻቀበ ነው፡፡ የአቶ ኢሳያስ አስተዳደርም ይህን ሁኔታ ለማዳፈንና የጸረ-ዴሞክራሲያዊነት

ሱሱን ለመወጣት በየጎጡ እስር ቤቶች ከፍቶ ኤርትራን የእሥር ቤቶች ሰንሰለት በማድረግ ሀገሪቱን "ወደ ትልቅ እስር ቤትነት" እየቀየራት ነው፡፡

አዎ! ሀገረ - ኤርትራ ሃሳብን በነጻነት የመግለጽና የእምነት ነጻነት የሌለበት ብቻ ሳትሆን፣ በሻዕቢያ ጦረኛና ፀረ -ዴሞክራሲያዊ ጠበል ያልተጠመቁ ጋዜጠኞች እንዲሁም ትላልቅ የሃይማኖት አባቶች በየመንደሮቹ ወደ ተገነቡት የእስር ቤት ሰንሰለቶች የሚወረወሩባት ሀገር ጭምርም ናት፡፡በቃ እስከወዲያኛው ሃሳባቸውን እንዳይገልጹ፣ ሃይማኖታቸውን በአደባባይ እንዳያከብሩ ፀጥ ይላሉ - ኤርትራውያኑ፡፡

የዴሞክራሲም ይሁን የፀሎት ድምጻቸው ሳይሰማ ጸጥ ይላል፡፡ ፀጥታውም በእስር አሊያም እስር ቤቶች ውስጥ በሚደረግ አሰቃቂ ግድያ ይደመደማል፡፡እናም እንደ ሰንሰለት የተያያዙት የሻዕቢያ እስር ቤቶች ግዳያቸውን ይጥላሉ፡፡

…አዎ! በኤርትራ ልሳነ - ምድር የዴሞክራሲና የሃይማኖት ነጻነት ታፍነው አምባገነንነትና ፀረ - ዴሞክራሲያዊነት "ሎሜ" እየረገጡ ነው - እስር ቤቶቹ ደግሞ የአቶ ኢሳያስንና እፍኝ የማይሞሉ ተከታዮቻቸውን ፍላጎት ማርኪያ "የምስጢር ኪስ" ሆነዋል፡፡ መረጃዎች እንዲያመለክቱት፣ በትንሿ ኤርትራ ውስጥ ድብቆቹን ሳያትት በግልጽ የሚታወቁ ከ37 በላይ እስር ቤቶች ይገኛሉ፡፡

ይህም ፀረ - ዴሞክራሲው የአቶ ኢሳያስ አስተዳደር በአንድ ወቅት እህል በማምረት "ሲንጋፖርና ታይላንድ ትሆናለች" ያላትን ሀገር ወደ "እስረኞች ማምረቻነት እየቀየራት መሆኑን በግልጽ የሚያመላክት እውነታ ነው፡፡ የሚሌኒየሙን የልማት ግብ ሙሉ ለሙሉ የሚያሳካው የሀገራችን ልማታዊ መንግስት የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶችን በየመንደሩ ሲከፍት፣ አስገራሚው የአቶ ኢሳያስ አስተዳደር ግን በየመንደሩ አዳዲስ እስር ቤቶችን ይገነባል፡፡ እኔ የምላችሁ እኚህ አቶ ኢሳያስ አፈወርቂ የሚሊየሙን የልማት ግብ የሚያሳኩት እስር ቤቶችን ለሁሉም ዜጋ በማዳረስ ነው እንዴ?ቂ.ቂ.ቂ....

ቀደም ሲል ከ37 በላይ መሆናቸውን የገለጽኩላችሁንና "ነጻነት" የወለደው ሰቆቃ ማስተናገጃ የሆኑትን እነዚህን እስር ቤቶችና በውስጣቸው የሚካሄደውን ዘግናኝ ትዕይንት ለመዘርዘር የቦታ ውስንነት ያግደኛል፡፡

ይሁንና ከፍተኛ ግፍ ከሚፈጸምባቸው እስር ቤቶች ውስጥ ጥቂቶቹን ለመጥቀስ ያህል፣ አደርሰር(ሳዋ)፣ ዓዲ ቀይህ፣ ዳህላክ ከቢር (ዳህላክ ደሴቶች) ኢራኢሮ (በአስመራና በምጽዋ መካከል)፣ ጋልዓሎ (ቀይ ባህር ዳርቻ) እና ሓዲሽ መዓስከር (ሱዳን ጠረፍ አቅራቢያ) ይገኙባቸዋል፡፡

በሀገሪቱ በግልጽ ከሚታወቁት ከ37 በላይ እስር ቤቶች መካከል በምሳሌነት የጠቀስኳቸውን የእነዚህን እስር ቤቶች ጭካኔ የተሞላበትን አሰራር መመልከት ርግጥም ሻዕቢያ "እጁን በእጁ የሚበላ" ምን ዓይነት ፀረ - ህዝብ ቡድን መሆኑን ፍንትው አድርጎ የሚያሳይ ነው፡፡

"አደርሰር" እየተባለ የሚጠራው እስር ቤት ሳዋ ወታደራዊ ማሠልጠኛው ውስጥ የሚገኝ ነው፡፡ እስር ቤቱ ሳዋ ውስጥ ወታደራዊ ትምህርት የሚወስዱ አሊያም የኤርትራ መከላከያ ሠራዊት ውስጥ ሲያገለግሉ የነበሩና ከአቶ ኢሳያስ አገዛዝ ጋር "ሆድና ጀርባ" የሆኑ ወይም "የሻዕቢያ ነገር በቃኝ" ብለው ያኮረፉ ወጣት ወታደሮች የሚታጎሩበት ነው።

በዚህ እስር ቤት ውስጥ አሰቃይ የግርፋት ዓይነቶች የሚፈጸሙ ሲሆን፤ ይህ ተግባር ለማከናወንም እስር ቤቱ ከመሬት በታች ውስጥ ለውስጥ የመግረፊያ ክፍሎች እንዲኖሩት ተደርጎ የተሰራ ነው፡፡

ብሔራዊ ውትድርና አገልግሎት አንሄድም ያሉ ወጣቶችና ቤተሰቦቻቸው የሚታሰሩበት የአስመራው "ዓዲ ቀይህ" እስር ቤትም፣ ታሳሪዎች ወደ ሌላኛው ሰንሰለት ዘግናኝ እስር ቤቶች እስከሚዘዋወሩ ድረስ መቆያ ቦታ ነው፡፡

በዚህ እስር ቤት እስረኞቹ ድብደባን፣ ስቃይን፣ የምግብ ክልከላን ወዘተ. አስቀድመው እንዲለማመዱ ይደረጋል፡፡ እናንተዬ … ነገሩ እንደ እኛው ሀገር ቅድመ - አንደኛ ደረጃ ትምህርት (መዋዕለ ህጻናት) መሆኑ ነው እንዴ?...

በአቶ ኢሳያስ አፈወርቂ ላይ የጻፈ፣ ያስጻፈ፣ የተናገረ ወይም ያስነገረ ወይም ሃሳቡን በነጻነት የገለጸ ወይም ለመግለጽ ያሰበ ጋዜጠኛ የሚታሰርበት እንዲሁም የሰውዬውን "ስውር ሰይፍ" የሚቀምስበትና አስመራ ውስጥ የሚገኘው "አጂፕ"

የሚሰኘው እስር ቤት፣ በአንድ ወቅት በአማካይ ከዘጠኝ የሀገሪቱ ጋዜጠኞች ውስጥ ስምንቱን አግቶ ፍዳቸውን ሲያዩበት የነበረ ቦታ ነው - እንደ ድንበር የለሽ ጋዜጠኞች መብት ተከራካሪ ቡድን የአንድ ወቅት ገለጻ፡፡

“አጂፕ” አስመራ ውስጥ “ከካፒቶል ሲኒማ ቤት” በስተጀርባና ከአቶ ኢሳያስ ቤተ - መንግስት ፊት ለፊት የሚገኝ ሲሆን፤ እስር ቤቱ ጋዜጠኞቹ ወደ ጠረፋማና ሞቃታማ ቦታ ከመወሰዳቸው በፊት ከባድ ድብደባና ስቃይ የሚፈጽምበት ስፍራ ነው፡፡ ይህን ለአቶ ኢሳያስ ቤተ-መንግስት ቅርበት ያለውን እስር ቤት ሳነሳ፣ አምባገነኑን የቀድሞ የኡጋንዳ መሪንና ራሳቸውን “ፊልድ ማርሻል” እያሉ የሚጠሩትን ኤዲ አሚን ዳዳን አስታወስኳቸው፡፡

አሚን ከአንድ ወቅት፣ የተቃዋሚዎቹን አንገት እየቆረጠ ፍሪጅ ውስጥ ያስቀምጡና ጧት፣ ጧት ከእንቅልፋቸው ሲነሱ “ደህና አደራችሁ?” በማለት የተቆረጡት አንገቶች መኖርና አለመኖራቸውን ያረጋግጡ እንደነበር ይነገራል፡፡

አቶ ኢሳያስም ጋዜጠኞቹን በአቅራቢያቸው የሚያስሩት መኖርና አለመኖራቸውን ለማረጋገጥ “የስቃይ ጩኸታቸው በደንብ ስላልተሰማኝ ጠበቅ አድርገህ ግረፍልኝ!” ለማለት ይሆን እንዴ?...

በዳህላክ ደሴቶች ውስጥ ከሚገኙት እስር ቤቶች አንዱ የሆነውና 800 እስረኞችን የመያዝ አቅም ያለው “ዳህላክ ከቢር” እስር ቤት የፖለቲካ እስረኞች የሚታጎሩበት ቦታ ነው፡፡ እስር ቤቱ ስምንት ትላልቅ ከብረት የተሰሩ መጋዘኖችን የያዘ ሲሆን፤ ከመሬት በታችም ለማሰቃያነት የሚያገለግሉ ድምጽ አልባ ክፍሎችም አሉት፡፡ ይህ እስር ቤት የሻዕቢያን የግፍ በትር በመፍራት ወደ ሊቢያና ግብጽ ጠፍተው የተሰደዱ ኤርትራውያን፣ ሀገራቱ ከሀገራቸው ሲያባርሯቸው የሚታሰሩበት ቦታም ነው፡፡

በዚህ ፅሑፍ ላይ የተመለከታችሁት ፎቶግራፍ፣ በዳህላክ ደሴቶች ውስጥ ከምድር በታች የሚገኝና ልዩ ስሙ “ናኩራ” እየተባለ የሚጠራ ቦታ ላይ የተዘጋጀው የአቶ ኢሳያስ ሌላኛው የግፍ ጽዋ መጋቻ መግቢያ በር ነው፡፡ የ“ናኩራ” እስር ቤት ፊት ለፊት እንጂ ጀርባው አይታወቅም - ምክንያቱም በታላቁ የቀይ ባህር የተከበበ ነውና፡፡

ማንም ሰው በዚህ እስር ቤት ውስጥ መግባት እንጂ መውጣት አይችልም፡፡ ይህን ጽሑፍ የሚያነብ ሰው፣ “አንድ መንግስት የራሱን ዜጎች በዚህ ዓይነት ሁኔታ ያሰቃያል” ብሎ ሊገምት አይችልም፡፡

ኤርትራ ውስጥ በተጨባጭ ያለው እውነታ ግን ይህ ነው፡፡...የሻዕቢያ ቱባ ባለስልጣናትና አለቃቸው ኤርትራውያንን በዚህ መልኩ ከምድር በታች በሚገኘው እስር ቤቶች እያሰሩና እያሰቃዩ ራሳቸውን  ከምድር በታች በሚገኘው የምጽዋው ቤተ - መንግስታቸው እግራቸውን አንፈራጠው በሰው ስቃይ ይደሰታሉ፡፡

አቶ ኢሳያስ ደረታቸውን ነፍተው የሚናገሩለትና የሚመኩበት ሌላው ዕውቁ አስር ቤታቸው “ኢራኢሮ”  ይባላል፡፡ በአሥመራና በምጽዋ  መካከል የሚገኘው ይህ የሻዕቢያው መሪ ተቃዋሚዎችን በግፍ የሚያስቃዩበት እሥር ቤት፣ ምንነቱ በይፋ እስከተገለጠበት ቅርብ ጊዜ ድረስ በምስጢራዊነቱ ነበር የሚታወቀው።

“እንኳንስ ዘንቦብሽ...” እንዲሉ አቶ ኢሳያስ በሥልጣናቸው የመጣባቸውን ሰው ሞቶ መቃብሩን ካላዩ በስተቀር እንቅልፍ አይወስዳቸውም፡፡ እናም ከዛሬ ዘጠኝ ዓመት በፊት እዚህ ቦታ ላይ ካሰሩዋቸው 35 ተቃዋሚዎቻቸ ውስጥ፣ 15ቱ ህይወታቸው ሲያልፍ በአይናቸው በብረቱ ተመልክተዋል፡፡

ተቃዋሚዎቻቸውን አምስት ትላልቅ ህንጻዎች፣ ሁለት መካከለኛ ማስቃያ ቤቶች እና ሦስት በሦስት ሜትር ስፋት ባላቸው 62 የኮንቴይነር ክፍሎች ውስጥ አጉረው በግርፋት የስቃይ ጽዋ የሚግቷቸው የሻዕቢያው መሪ፣ ግለሰቦቹ በቂ ምግብ እና ህክምና እንዳያገኙ እንዲሁም በኃይለኛ ሙቀት ታፍነው እንዲሞቱ አድርገዋቸዋል፡፡

ለህልፈተ - ህይወት ከተዳረጉት መካከል የኤርትራው ምክትል ፕሬዚዳንት የነበሩት አቶ መሃመድ ሸሪፎ እንዲሁም ጄኔራል ዕቁብ አብርሃ እና በእስር ላይ የነበሩ ሦስት ጋዜጠኞች ይጠቀሳሉ፡፡

በዚህ እስር ቤት  ውስጥ ወደ አካለ ጎዳዶሎነት ከተሸጋገሩት ዘጠኝ ሰዎች መካከል፣ ኢትዮ-ኤርትራ ጦርነት ወቅት የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር የነበሩትና የአልጀርሱን ስምምነት የተፈራረሙት አቶ ኃይለ ወልደተንሳይ አንዱ ናቸው፡፡ እኚህ

ሰው በአሁኑ ወቅት ሙሉ በሙሉ አይነ ስውር የሆኑ ሲሆን፤ በጤንነታቸው የተሻሉ ናቸው የሚባሉት እስረኞች ደግሞ ሃያ አራት ሰዓት ሙሉ በእግረ ሙቅ ካቴና እግር ተወርች ታስረው ቀስ እያሉ እንዲሞቱ እየተደረጉ ነው፡፡

በቀይ ባህር ዳርቻ አቅራቢያ ጭው ባለ በረሃ ላይ የተገነባው "ጋልዓሎ" እስር ቤትም፣ "ጥፋተኛ" ተብለው በሻዕቢያ የተፈረደባቸው ወታደሮች በግዳጅ የጉልበት ሥራ የሚያካሂዱበት ቦታ ነው፡፡ እዚህ እስር ቤት ውስጥ በርካታ "ተማሪ - ወታደሮች" በረሃብና በሙቀት ምክንያት መሞቻቸው ይታወቃል፡፡

ሱዳን ድንበር አቅራቢያ የሚገኘው የሻዕቢያው "ሓዲሽ መዓስከር" እስር ቤትም ከዚህ የተለየ አይደለም፡፡ ፍጹም ኢ-ሰብዓዊ ተግባር ይከናወንበታል፡፡ ነገሩ "ማን ይናገር የነበረ..." እንዲሉ ነውና፣ ኤርትራዊ አቶ ሙሴ ሐድጉ እንዲህ ይገልጹታል፡፡ "...ግርፋትና ስቃይ የእስር ቤቱ የዕለት ተዕለት ተግባር ነው፡፡

በዚህም በርካታ ወጣቶች ለዕብደትና ለሞት ተዳርገዋል..." በማለት በቅርቡ ለመገናኛ ብዙሃን ተናግረዋል፡፡ የታሰረ ልጃቸውን ፍለጋ ሄደው በሻዕቢያ ባለስልጣናት ወደ እስር ቤት የተወረወሩት አቶ ሙሴ፣ጥርብ ድንጋይ በመፍለጥ፣ ዕቃ በመጫንና በማውረድ፣ በግንባታ ስራዎች እንዲሁም በሽንት ቤት ጠረጋ ስራዎች ተሰማርተው መቆየታቸውን በስደት ከሚገኙበት ሱዳን በጸጸትና በሐዘን ይናገራሉ፡፡

"ልጆቻችን የተሰውለት ነጻነትስ የታለ?" ሲሉም ራሳቸውን በራሳቸው ይጠይቃሉ..." አዎ! የአቶ ሙሴ ጥያቄ ትክክለኛ ቢሆንም፣ "ነጻነቱ" ግን ሰቆቃን ወልዶ በማጎሪያዎቹ ውስጥ እንደ ርሳቸው ከመሳሰሉ እስረኞች ጋር አብሯቸው ተከቷል፡፡

ማንም የዚህ ጽሑፍ አንባቢ፤ "እንደ ሰንሰለት በተያያዙት በእነዚህ የሻዕቢያ የአፈና እስር ቤቶች ውስጥ የሚገኙት ታሳሪዎች ፍርድ ቤት ቀርበው ቅጣት የተወሰነባቸው ናቸው" ብሎ ካሰበ ርግጥም ያ ሰው የዋህ ነው፡፡

የአስመራው መሪና ጥቂት ግብረ -አበሮቻቸው በሚመሩት ሀገር ውስጥ ፍርድ ቤትና ህጋዊ አሰራርን መመኘት "ከዝንብ ማርን የመጠበቅ" ያህል ነው፡፡ ህዝባዊ መንግስት፣ ዴሞክራሲ፣ ህግና ስርዓት እንዲሁም የህግ የበላይነት የሌለበት፣ ዜጎቿ እንደ

“ክብት” እየተነተቱ ወደ “ጉረኖ” የሚነዱባትና ስለምንም ነገር እኩልነት የማይነገርበት ብሎም መንግስት የራሱን ዜጎች የሚያተራምስባት ታዳጊዋ ሀገር ኤርትራ ሁሉም ነገር የሚታቀደው፣ የሚሰራውና አፈጻጸሙ የሚነገረው በአንድና በአንድ ሰው ብቻ ነው - በአቶ ኢሳያስ፡፡

እርግጥ ነው አቶ ኢሳያስ ከሳሽ፣ ፈራጅ፣ አቃቤ ህግ፣ አሳሪና ገዳይ ናቸው፡፡ እኚህ ሰው በዚያች ትንሽዬ ሀገር ውስጥ የሚያምኑት ሰው የለም-ሁሉንም ይጠራጠራሉ፡፡ እናም አይከሱም፣ ፍርድ ቤትም አያቆሙም፡፡ ግና ይፈርዳሉ፣ ያስራሉ፣ ይገድላሉ፣ ያስገድላሉ፣ “ከአንድ ብርቱ፣ ሁለት መድኃኒቱ” የሚለው ሀገርኛ አባባል በሻዕቢያው መሪ ፊት ነውርና ውግዝ ሆኖ ነው የሚታየው፡፡…

…ታሪክን ወደ ኋላ ስንመልሰው፣ ከዛሬ 23 ዓመት በፊት “የኤርትራ ህዝብ ለነጻነቱ ታገለ” የሚል አባባል በድርሳንነት ተከትቦ እናገኛለን፡፡ ከ”ነጻነት” በኋላም ያ ህዝብ ምርትና ምርታማነትን በማሳደግ የእህል ማከማቻ መጋዘኖችን እንጂ፣ የ”ነጻነቱ” ወሮታ ሆኖ ራሱ በሰው ማጎሪያ መጋዘኖች ውስጥ ቤዛ እሆናለሁ ብሎ አስቦም አያውቅም፡፡

የኤርትራው መሪ ግን እህልን ሳይሆን ሰውን በማጎር በምስራቅ አፍሪካ ግንባር ቀደም ሆኑ፡፡ ዛሬ “ታይዋንና ሲንጋፖር” ምርቶቻቸውን ወደ ውጭ ሲልኩ፣ ዝነኛው የሻዕቢያ መሪ ግን ኤርትራዊያንን በማፈን ሽብርን ሀገራቸው ውስጥ እያመረቱ ወደ ውጭ ይልካሉ፡፡

እናም ዛሬ ከሀገረ -ኤርትራ ‘ነፃነቴ ተነጠቀ’ ብሎ የሚጠይቅ ዜጋ ለቁጥር ከሚታክቱት ግልጽና ስውር እስር ቤቶች ውስጥ የአንዱ ሰለባ መሆኑ አይቀርም፡፡ ይህም በዚያች ሀገር የሚኖረውን ዜጋ ለስደት እየዳረጉት ገሚሱ ባህር ላይ ለህልፈተ-ህይወት ይዳረጋሉ። እርግጥ ይህን ሰቆቃ ‘በቃ’ ማለት ያለበት ወንድም የሆነው የዚያች ሀገር ህዝብ ነው—የእርሱን ሚና ተክቶ ማንም ነፃነቱን ሊያጎናፅፈው አይችልምና።